በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፳


**መምህር፦ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

*ቦታ፦* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ኅዳር ፲፩ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫

- እስካሁን እንደተመለከትነው ነህምያ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም መነቃቃትን እንደፈጠረ ቅጥሮቹንም እንደሠራ ተምረናል፡፡
- በሥራ ገበታችንም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ያለ መነቃቃትን (መነሳሳትን) ለማምጣት ሦስት ነገሮች የግድ ያስፈልጋሉ፡፡ እነርሱም መልካም መሪ፣ እውቀት (ትምህርት፣ እውነት፣ የእግዚአብሔር ቃል... ***ሆሴዕ 4:6*** ‹‹ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።›› እንዳለ)፣ እና ሕዝብ (ምዕመናን) - ሕዝብን (ምዕመናንን) ማሳተፍ (ማስተባበር) ናቸው፡፡
- ለቤተ ክርስቲያን፣ ለተቋማትም ይሁን ለማንኛውም ነገር መነቃቃትን/መነሳሳትን (Revival) ለማምጣት እነዚህ ሦስቱ የግድ አስፈላጊዎቻችን እንደሆኑ ልብ እንበል፡፡
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ፣ አባ ኢየሱስ ሞዓ፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እና ሌሎቹም በዘመናቸው የምናስተውለውን መንፈሳዊ ሥራ በመሥራት ሌሎችም የበለጠ እንዲሠሩ ያነሳሱት/ያነቃቁት እነዚህን ሦስቱን ይዘው ነው፡፡
- በ19ኛው መጨረሻና በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ የነበረው ፖፕ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ በግብጽ ኮፕት ቤተ ክርስቲያን እስከ ዛሬ ድረስ ተስፋፍቶ ለሚታየው መነሳሳት ምክንያት የሆነ አባት ነው፡፡
- ፖፕ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ በትምህርት እጅግ የሚያምን በቤተ ክርስቲያኒቱ ያለውንም ትምህርት ለማስፋፋት የቻለ ነበር፡፡
- ፖፕ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ሐቢብ ጊዮርጊስን መረጠና የእስክንድርያ የቶዎሎጂ ትምህርት ቤት ኃላፊ አደረገው፡፡ ሐቢብ ጊዮርጊስም ሕይወቱን ለትምህርትና ለእውቀት የሰጠ ነበር፡፡

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፭</u>

- ሐቢብ ጊዮርጊስም መላ ትኩረቱን ትምህርት ላይ በማድረግ አቡነ ሲኖዳን ደቀ መዝሙር አድርጎ አፈራ፡፡ አቡነ ሲኖዳም የትምህርት ጳጳስ ሆነው ተሾሙ፡፡ አሁን በግብጽ ኮፕት ቤተ ክርስቲያን የምናየው ለውጥም የመጣው በዚሁ መንገድ በቄርሎስ ፭ኛ ምክንያትነት ሐቢብ ጊዮርጊስ በመገኘቱ ነበር፡፡
- በግብጽ ኮፕት ቤተ ክርስቲያን አሁን የምናየውን ከፍተኛ ለውጥ ያመጡት ፖፕ ሲኖዳም ከመንፈሳዊነት ጋር በተዋሐደ ትምህርትና ዕውቀት ምዕመናን የተሳተፉበት አመራር በመስጠት ከልብ የሚያምኑ ስለነበሩ ነው፡፡
- ምዕመናንን በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማቅረብና ማሳተፍ፣ ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ አምነው የድርሻቸው እንዲወጡ ማድረግ መነሳሳትን ይፈጥራል፤ ይህንም ማሳካት መልካም መሪ መሆንና መማርና ማወቅን ይፈልጋል፡፡
- ነህምያ መልካም መሪ በመሆን ከቅጥሩ ሥራ በተጨማሪ ታሪካዊ መነሳሳትን (መነቃቃት) በአይሁድ / በእሥራኤላውያን ዘንድ ፈጥሯል፡፡ ምዕራፍ ሰባት የሚያስተምረንም ይህንኑ ነው፡፡
- ‹‹ እንዲህም ሆነ ቅጥሩ ከተሠራ በኋላ፥ ሳንቃዎቹንም ካቆምሁ በኋላ፥ በረኞቹና መዘምራኑ ሌዋውያኑም ከተሾሙ በኋላ፥ ወንድሜን አናኒንና የግንቡን አለቃ ሐናንያን በኢየሩሳሌም ላይ ሾምኋቸው እርሱም እውነተኛ ከሌሎቹም ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበረ።›› ***<u>ነህ 7፡1-2፡፡</u>***
- ሁሉም ነገር በኢየሩሳሌም መልክ ከያዘ በኋላ ነህምያ ራዕዩን ከግብ ለማድረስ፣ ከበላይም ሆኖ በመሪነቱ እየተቆጣጠረ ለመቀጠል በሥሩም አስተዳዳሪ (Who Does What) ለመሾም ስለወደደ የከተማይቱን ኃላፊነት ለሁለት ሰዎች ሰጠ፡፡ የሁለቱም ሰዎች መለያቸው እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፭

- መልካም መሪ ማንን እንደሚመርጥ ተመልከቱ! እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን!!!
- ‹‹እኔም። ፀሐይ እስኪሞቅ ድረስ የኢየሩሳሌም በሮች አይከፈቱ እነርሱም ቆመው ሳሉ ደጆቹን ይዝጉ፥ ይቈልፉም ከኢየሩሳሌምም ሰዎች አንዳንዱን በየተራው አንዳንዱንም በየቤቱ አንጻር ጠባቆችን አስቀምጡ አልኋቸው። ከተማይቱም ሰፊና ታላቅ ነበረች በውስጥዋ የነበሩ ሕዝብ ግን ጥቂቶች ነበሩ፥ ቤቶቹም አልተሠሩም ነበር። አምላኬም ታላቆቹንና ሹማምቱን ሕዝቡንም ሰብስቤ እቈጥራቸው ዘንድ በልቤ አደረገ አስቀድመው የመጡትን ሰዎች የትውልድ መጽሐፋቸውን አገኘሁ፥ በእርሱም እንደዚህ ተጽፎ አገኘሁ። የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ከማረካቸው ምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ወደ እየከተማቸው የተመለሱት የአገር ልጆች እነዚህ ናቸው።›› ***ነህ 7፡3-6፡፡*** እያለ ሐረጋቸውን እስከ ቁጥር 73 ይዘረዝራል፡፡
- ቅጥሩ ተሠርቷል፣ ሁሉም ነገር ተከናውኗል፤ ታዲያ የትውልዱን ሐረግ ዘርዝሮ መጻፍ ስለምን አስፈለገው፡፡ ይህም ማለት የኛን አያት፣ ቅድመ አያት፣ ቅመ አያት፣… መቁጠር ማለት ነው፡፡
- ነህምያ ይህን ያደረገው ሁሉን በአግባብ ለማከናወን ነው፡፡ በምናሠራው ሥራ አንዳንድ ሠራተኞችም ሆኑ አሠሪዎች ሥራው በርካሽ መሠራቱ ላይ፣ ሌላው እኛ መደሰታችን (መርካታችን) ላይ፣ ሌሎቹ ፍጥነት ላይ፣ ወዘተ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡
- ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ለቁርስ፣ ምሳና እራት ይኖራሉ፡፡ ነህምያ ግን ትኩረቱ ሥራው በትክክል መሠራቱ ላይ ነበር፡፡ ሐረግ መቁጠሩ ያስፈለገው ለጌታችን የትዉልድ ሐረግ ስለሚያስፈልግ ነው፡፡ ነህምያ ባይጽፍልን ኖሮ ጌታችን የተገኘበትን ሐረግ መቁጠር ክፍተት ባገኘው ነበር፡፡
- ነህምያ ይህንም አስመልክቶ ‹‹እግዚአብሔር በልቤ አኖረው›› አለን፡፡ አስተምረን ላታነቡት ትችላላችሁ ግን ለምን አትመን/ኢሜይል/አፕሎድ እናደርግላችኋለን - እግዚአብሔር በልባችን ስላኖረው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፰

- የትውልድ ሐረጉን ነገር መጻፍ ከባድ ነው፤ በቀላሉ ሲታሰብ ምን ይጠቅማል የሚያሰኝ ቢሆንም ነህምያ መሪ ነውና ጻፈው:: መሪ ደግሞ እግዚአብሔር በልቡ ያኖረውን ከማድረግ አይመለስም::
- ሚስቱ ‹‹ሥራውን ጨርሰናል በል አሁን ወደ አዋሳ፣ ላንጋኖ… እንሂድ ደስም ይበለን… ›› ምን የምትለው ይመስላችኋል? ነህምያ ግን አይሆንም አንድ ነገር ይቀረኛል እርሱም የትውልድ ሐረጉን ነገር መጻፍ ነው አለ:: ለምን ያስፈልጋል? እግዚአብሔር በልቡ ስላኖረው፤ ማድረግ ያለበት ትክክለኛ ነገር ነውና አደረገው::
- ምዕራፍ ስምንት ‹‹ሰባተኛውም ወር በደረሰ ጊዜ የእስራኤል ልጆች በከተሞቻቸው ነበሩ። ሕዝቡም ሁሉ በውኃው በር ፊት ወዳለው አደባባይ እንደ አንድ ሰው ሆነው ተሰበሰቡ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ያዘዘውን የሙሴን ሕግ መጽሐፍ ያመጣ ዘንድ ጸሐፊውን ዕዝራን ተናገሩት።›› ***ነህ 8:1::***
- ወንዶችና ሴቶች በተሰበሰቡበት አደባባይ በሰባተኛው ወር መጀመሪያ በውኃው በር ፊት ወዳ ለው አደባባይ እንደ አንድ ሰው ሆነው ተሰበሰቡ:: እግዚአብሔርም ለእስራኤል ያዘዘውን የሙሴን ሕግ መጽሐፍ ያመጣ ዘንድ ጸሐፊውን ዕዝራን ተናገረዉ::
- እውነተኛው መነሳሳትና መነቃቃትም ይህ ነው!!! ቅጥሩን ሠርቷል አሁን ደግሞ ነፍሳቸውን እየገነባ ነው::
- ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን መሥራት አቁመው ሰውን (ነፍሳትን) ወደ መገንባት የተመለሱባትን የቤተ ክርስቲያንን ነገር እናውቃለን? ነህምያ ግን አስተዋይ መሪ ነበር፤ ቅጥሩን ሠራና ‹‹ሥራውን በ52 ቀናት ፈጽመናል፣ ታላቅ ታሪክ ነው፤ አሁን ተሰብሰቡ›› አለና ነፍሳቸው የምትገነባበትን አሳያቸው::
- ሕዝቡ በእጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ አልያዙም ነበርና የሙሴን ሕግ በካህኑ በዕዝራ አስነበበላቸው::
- የዕዝራ ሥራው ሕዝቡን ማስተማር ነውና ጠርቶ መጥተህ በዚህ ቁም ሕዝቡንም በዚሁ ዙሪያ እሰበስብልሃለሁ፣ አንተም ቀኑን ሁሉ ታነብላቸዋለህ ሕዝቡም ይሰማሉ አለው::

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፫</u>

- የራቀ ሰው ሁሉ መጥፎ እንደሆነ አድርገን አናስብ፤ ከነዚህ መካከል ያለዕውቀት የጠፉ አሉና፡፡ ጌታችንም እነዚህን (የጠፉ) በጎች ብሎአቸዋል፡፡ ለምን በጎች አላቸው - ምንም ስለማያውቁ፡፡ ***<u>ሉቃ 15::</u>***
- ሰዎች ሕይወት የሚገኝበትን ቃል ለመማር ሰነፎች ናቸው፡፡ ***<u>ካል ጢሞ 4:1-4::</u>*** ሲለሚወቀሱ መስማት አይሹም፡፡ የሰሙት ግን አብዝተው አንብተዋል - አልቅሰዋል፡፡
- እነዚህም ሕዝቦች ተማርከው፣ ጠፍተው ነበር፤ ስለማይሰሙ፣ ስለማያነቡ፡፡ በሕይወታቸው ታላቅ ለውጥ የሚያደርጉ ሰዎች ለውጡ የእግዚአብሔርን ቃል መማር፣ ማንበብ በመጀመራቸው የመጣ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሕይወት፣ ቁም ነገር አለና፡፡
- ታላቁ መሪም ይህን በማወቅ ቅጽር ብቻ አይደለም ነፍስም መገንባት አለበት አለ፤ ከሁሉም በላይ ነፍሳቸው የሚገነባውም የእውነትን ቃል - የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ ነው አለና ዕዝራን አግኝቶ ቀኑን ሙሉ እንዲያነብላቸው አዘዘው፡፡
- ነህምያ ‹‹መሪ ሁሉ አንባቢ ነው›› አለ እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ያነብ ነበርና፡፡
- እግዚአብሔርም ‹‹የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።›› ***<u>ኢያ 1:8::</u>*** ለታላቁ መሪ ለኢያሱ የነገረው ይህንኑ ነበር፡፡ ነገር ሁሉ እንዲከናወንልህ ቃሌን ቀንና ሌት አጥና በማለት፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል የማያጠና የማይማር የማያውቅም ለጥፋት ራሱን ያዘጋጀ አላዋቂ ነው፡፡
- ነህምያ ራሱ ስለምን አላነበበላቸውም? ምክንያቱም በአመራር በሚታወቀው ያልተማከለ አሠራር የሚያምን፣ ሁሉን ራሴ ላድርገው የማይል፣ ከተማይቱንም ለወንድሙ የተወ፣ መጻሕፍትንም ለማንበብ ለካህናት የተሰጠውን የሚያምንና የሚቀበል ስለነበር ነው፡፡ እውነተኛ መሪ ከሌሎችም ይማራል፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፰

- ‹‹ዕዝራም በሕዝቡ ሁሉ ላይ ከፍ ብሎ ሕዝቡ ሁሉ እያዩ መጽሐፉን ገለጠ በገለጠውም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ። ዕዝራም ታላቁን አምላክ እግዚአብሔርን ባረከ ሕዝቡም ሁሉ እጃቸውን እየዘረጉ። አሜን፥ አሜን ብለው መለሱ። ራሳቸውንም አዘነበሉ፥ በግምባራቸውም ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ። ደግሞ ኢያሱና ባኒ፥ ሰራብያ፥ ያሚን፥ ዓቁብ፥ ሳባታይ፥ ሆዲያ፥ መዕሤያ፥ ቆሊጣስ፥ ዓዛርያስ፥ ዮዛባት፥ ሐናን፥ ፌልያ፥ ሌዋውያኑም ሕጉን ያስተውሉ ዘንድ ሕዝቡን ያስተምሩ ነበር ሕዝቡም በየስፍራቸው ቆመው ነበር። የእግዚአብሔርንም ሕግ መጽሐፍ አነበቡ ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፥ ሕዝቡም የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር።›› ***ነህ 8፡5-8፡፡***
- **ማንበብ ብቻ አይደለም ያስተውሉ ነበር፡፡ ሲሰሙም ቆመው፣ በመጸለይ፣ በመስገድ ነበር፡፡ ይህ ታዲያ በቤተ ክርስቲያናችን ወንጌል ስናነብ የምናደርገው አይደለምን? ቤተ ክርስቲያናችን ወንጌልን ማንበብ ብቻ አይደለም ትጸልየዋለች፡፡ በጠረጴዛ ላይ ሳይሆን በአትሮንስ አድርገን ቆመን ስናነበው ሕዝቡም ቆመው ይሰማሉ፡፡ ስናነበውም ዜማ በተቀላቀለበት መንገድ ጸሎት አድርገን - እናነበዋለን፡፡ በዚህም መንገድ መንፈስ ቅዱስ ከኛ ጋር ሆኖ እናነበዋለን እንሰማዋለን፡፡**
- ‹‹ሐቴርሰታ ነህምያም ጸሐፊውም ካህኑ ዕዝራ ሕዝቡንም የሚያስተምሩ ሌዋውያን ሕዝቡን ሁሉ። ዛሬ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ቀን ነው አታልቅሱ እንባም አታፍስሱ አሉአቸው ሕዝቡ ሁሉ የሕጉን ቃል በሰሙ ጊዜ ያለቅሱ ነበርና። እርሱም፡- ሂዱ፥ የሰባውንም ብሉ፥ ጣፋጩንም ጠጡ፥ ለእነዚያም ላልተዘጋጀላቸው እድል ፈንታቸውን ስደዱ ዛሬ ለጌታችን የተቀደሰ ቀን ነው የእግዚአብሔርም ደስታ ኃይላችሁ ነውና አትዘኑ አላቸው። ሌዋውያንም። ቀኑ የተቀደሰ ነውና ዝም በሉ፥ አትዘኑም ብለው ሕዝቡን ሁሉ ጸጥ ያደርጉ ነበር። ሕዝቡም ሁሉ የተነገረላቸውን ቃል አስተውለዋልና ሊበሉና ሊጠጡ እድል ፈንታም ሊሰድዱ ደስታም ሊያደርጉ ሄዱ።›› ***ነህ 8፡9-12፡፡***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፰

- ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ አለቀሱ፡፡ በሰንበት ት/ቤት ስናስተምር ሕጻናቱ ሲያለቅሱ አታልቅሱ ብለናቸው እናውቃለን? ስለ ኃጢአታቸው ነውና ያልቅሱ ነው የምንለው?
- በቤተ ክርስቲያናችን የምናደርገው ይህንኑ ነው፡፡ የሐዘን (የጾም)፣ የደስታ (የበዓላት) ቀናትና ለነዚህም የአምልኮት (የአገልግሎት) ሥርዓት አለን፡፡
- አንዳንድ ሰዎች አንዱንም እንኳ አልሰራሁም ብሎ ያለቅሳሉ - በእንባ እንዲቀጥሉ ይበረታታሉ፤ ሌላው ደግሞ ንስሐ ገብቶ - ቅዱስ ቁርባን ተቀብሎ ተስተካክሎ ደስ ብሎት ያለቅሳል - በደስታ ነውና ተው ይባላል፡፡
- ወላጆች ልጆቻችን አጥፍተው ጥፋታቸውን ሲያውቁ - አናስጨንቃቸው እናበረታታቸው እንጂ፡፡ ወላጆች ሆይ! ለልጆቻችሁ ተስፋ ስጡአቸው፡፡ አስቀድመው ጥፋተኝነት ስለተሰማቸው ከፍ እናድርጋቸው፡፡
- መጽሐፈ ነህምያ ከምዕራፍ አንድ እስከ ስድስት የሚናገረው ቅጥሩን ስለመሥራት ነው፡፡ ከምዕራፍ ሰባት እስከ አሥራ ሦስት ግን የሰው ነፍስ የሚገነባባቸውን ሦስት ትእዛዛትን እናገኛለን፡፡
- ከዚህ በኋላ ነህምያ ዕዝራ ሕዝቡን በመንፈሳዊነት ይመራ ዘንድ አስቀድሞት እናገኛለን፡፡
- እንግዲህ መጽሐፈ ነህምያ ስለ አመራር ክህሎት ከምናነባቸው አሥር መጻሕፍት የሚበልጥ መጽሐፍ ነው፡፡ ከምዕራፍ ሰባት እስከ አሥራ ሦስት ዕዝራ ሕዝቡን በመንፈሳዊነት ወደ መንፈሳዊነት እንዴት እንደመራ እንመለከታለን፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፰

- ‹‹በሁለተኛውም ቀን ከሕዝቡ ሁሉ የአባቶች ቤቶች አለቆች ካህናቱም ሌዋውያኑም የሕጉን ቃል ይተረጉምላቸው ዘንድ ወደ ጸሐፊው ወደ ዕዝራ ተሰበሰቡ። በሰባተኛውም ወር ባለው በዓል የእስራኤል ልጆች በዳስ ይቀመጡ ዘንድ በከተሞቻቸውና በኢየሩሳሌምም። ወደ ተራራ ሂዱ የዘይትና የበረሀ ወይራ የባርሰነትም የዘንባባም የለመለመውን ዛፍ ቅርንጫፍ አምጡ፥ እንደ ተጻፈውም ዳሶችን ሥሩ ብለው ይናገሩ ያውጁም ዘንድ እግዚአብሔር በሙሴ እጅ እንዳዘዘ በሕጉ ውስጥ ተጽፎ አገኙ። ሕዝቡም ወጥተው አመጡ እያንዳንዱም በቤቱ ሰገነት ላይ፥ በአደባባዩም ላይ፥ በእግዚአብሔርም ቤት አደባባዩ ላይ፥ በውኃውም በር አደባባይና በኤፍሬም በር አደባባይ ላይ ዳስ ሠራ። ከምርኮም የተመለሱት ማኅበር ሁሉ ዳስ ሠሩ፥ በዳሱም ውስጥ ተቀመጡ። ከነዌም ልጅ ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ እስከዚያ ቀን ድረስ የእስራኤል ልጆች እንዲህ ያለ አላደረጉም ነበር። እጅግም ታላቅ ደስታ ሆነ። ከመጀመሪያውም ቀን ጀምሮ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ዕለት ዕለት የእግዚአብሔርን ሕግ መጽሐፍ ያነብብ ነበር። በዓሉን ሰባት ቀን ያህል አደረጉ በስምንተኛውም ቀን እንደ ሕጉ የተቀደሰ ጉባኤ ነበረ።›› ***ነህ 8፡13-18።***

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org